# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች ያተረጓጎም ስልት

*ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች፥ ፩ኛ:" አብጅ"*
*፪ኛ: "ጠብቅ"*

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ nigatuasteraye@yahoo.com

*ሐምሌ ፪፫ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.*

*ለሌሎች የቂሲስ አስተራየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለውን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ፥*
***http://www.medhanialemeotcks.org/***

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች ያተረጓጎም ስልት

## *ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች፥ ፩ኛ:" አብጅ"*
## *፪ኛ: "ጠብቅ"*

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ** nigatuasteraye@yahoo.com

*ሐምሌ ፳፫ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.*

# የአባቶቻችን የአተረጓጎም ስልት

ወደ አባቶች ሊቃውንት አተረጓጎም ስልት (ከአሁን በፊት በጻፍኩት መሰረት፥ http://www.medhanialemeotcks.org/pdf/Hermeneutics-Final.pdf ) ቀጥታ ከመሄዳችን በፊት፥ ለመግቢያ ያመቸን ዘንድ አበው የሚሉትን መጥቀስ እፈልጋለሁ:: ዓቢዩንና ዋቢውን (አብነቱን) ነገር መስለው ከሚቀርቡ ሠርጎ ገብ እንግዳ ነገሮች ለመለየት "እንደ እንግዳ ደራሽ፥ እንደ ውሐ ፈሳሽ አይደለም" ይላሉ:: የዘመኑ የስነ ጽሑፍ ሊቃውንትም ከዚህ አባባል ያልራቀ መመሪያ የስነ ጽሑፍ ስልት አላቸው:: እነሱም ለሚከተለው ትውልድ ቀምረው ያስቀመጧቸው በቅደም ተከተል ከዚህ በታች የተገለጹት ናቸው::

**፩ኛ ነቅዕ** (First sources) የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት
**፪ኛ ፈለግ** (Second resources) መጻሕፍተ ሊቃውንት (*ሃይማኖተ አበው*)
**፫ኛ አሥራግ** (Third resources) ከነቅዕና ከፈለግ መጻሕፍት ሳይርቁ በየጊዜው የተጻፉ

አባቶች እንደሚሉት *ነቅዕ* የሚባሉት የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት ናቸው:: *ፈለግ* የሚባሉት ከብሉያቱና ከሐዲሳቱ የመነጩት ከሐዋርያት ቀጥለው እስከ ፲ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ሊቃውንት፥ በዘመናቻው ለተፈጠሩት እንግዳ ትምህርቶች የሰጧቸው መልሶች፥ የኦርቶዶክስ ተዋህዶን መሠረታዊ ነገረ መለኮት የሚገልጹ ናቸው:: እነዚህ የተለያዩ የመልስ ጦማሮች፥ በብራና ተጽፈው ባንድነት ተጠርዘው በመበጀት ለብዙ ዘመን አባቶች ሲጠቀሙባቸው ቆይተዋል:: የመጀመሪያው ፓትርያርካችን አቡነ ባስልዮስ ለመጀመሪያ ጊዜ ባሳተሙት ጊዜ "ዋናዎቹ ጥንታውያን ሊቃውንት ይህን የሃይማኖተ አበው ትምህርት በቃልም ሆነ በጽፈት በዘመናቸው ለነበሩት ምዕመናንና ለተከታዩ ትውልድ" ሲአስተምሩት እንደኖሩ ገልጸው፥ "ሃይማኖተ አበው ማለት ከአባቶቻችን ተያይዞ ለልጆች የደረሰ ወደፊትም የሚተላለፍ ማለት ነው እንጅ፥ አባቶች ሲአልፉ አብሮ የሚአልፍ አይደለም" በማለት በተናገሩት በአደራ ቃላቸው ይህን መጽሐፍ አስረክበውናል::

በቅዱሱ አባታችን ፈቃድ የታተመው ይህ ሃይማኖተ አበው የሚባለው መጽሐፍ፥ በምዕ ፱፴፩ በገጽ ፮፻፫ የተጠቃለለ ነው:: ብሉያቱንና ሐዲሳቱን በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ነገረ መለኮት ግንዛቤ የቀረጸ መጽሐፍ ነው:: ሁሉንም አኀት አብያተ ክርስቲያናት የሚአስተሳስር ነው:: ፲፬ የቅዳሴ መጽሐፎቶቻችንም በነዚሁ ሊቃውንት የተደረሱና በዚሁ መጽሐፍ የተካተቱ ናቸው:: ከነዚህ ጋራ ተደማምረው *አሥራግ* የሚሏቸው ከ፹፩ በላይ የሆኑ ሌሎች ብዙ መጻሕፍቶችም አሉን:: ከዚያም ወዲህ ለትምህርትና ለተግሣጽ የሚጠቅሙ ያለፉና በሕይወት ያሉ ሊቃውንት አባቶች ከነቅዕ፥ ከፈለግና አሥራግ ሳይርቁ የጻፏቸው ውሂዛት መጻሕፍቶች

አሉን::

በዘመናችን የሚገኙ አንዳንድ ጸሐፊወች የቤታችን መሠረታዊው እሐሳብ ስለሌላቸው፥ በሚጽፏቸው መጽሐፎቻቸው ከውጭ የሰሙትን ሁሉ በመከተት የኦርቶዶክሱን መሠረታዊ እምነትና የመጽሐፉን ሕልውና እንዳልነበረ ለማድረግ እየሞከሩ ናቸው:: ቤተ ክርስቲያናችን በጥንታዊውና ባልተበረዘው ጉባዔዋ ቀርጻ ያሳደገቻቸው በሕይወት የሚኖሩ ሁሉ፥ እንደ ቅዱስ አባታችን አቡነ ባስልዮስ ይህችን ዓለም በሞት እስኪሰናበቷት ድረስ የመጠበቅ ኃላፊነት እዳና የሞራል ግዴታ አለባቸው::

ከላይ ከተጠቀሱት አንቅዕት፥ አፍላግና አሥራግ ርቀው የገድል፥ የድርሳን፥ ወይም በሮማ ካቶሊክና በፕሮቴስታንት ጸሐፊዎች የተጻፈውን እየቀላቀሉ ለነገረ መለኮት የሚጠቅሱ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ውጭ የሆኑና መገሰጽ ያለባቸው ናቸው:: አባቶቻችንና እናቶቻችን ወደላሊበላ፥ ወደ አክሱምና ወደሌሎችም የተቀደሱ መካናት በሚአደርጉት የምናኔ ጉዟቸው፥ ያንጎራጎሯቸውን ሁሉ እየጻፉና እያተሙ ያስቀመጧቸው፥ የትዝታ እንጉርጉሮዎች ስለ ነገረ መለኮት፥ ስለ እመቤታችንና ጻድቃን ሰማእታት፥ ስለመላእክት ምስክርነት ሊጠቀሱ አይገባም:: ተጓዥ ተሳላሚዎች በመንፈስ ጥማት ተቃኝተው በጉዟቸው ያንጎራጎሯቸው በመሆናቸው ብናከብራቸውም፥ ሊቃውንት በነገረ መለኮቱ ሚዛን መዝነው፥ ከቀሩት አኀት አብያተ ክርስቲያናትም ግንዛቤ ጋራም አገናዝበውና አስማምተው የተቀበሏቸው ባለመሆናቸው፥ አባቶቻችን ወደነገረ መለኮቱ እንዲቀርቡ አይፈቅዱም:: ከጉባዔዎቻቸውም ውጭ ናቸው:: ይህ ሁሉ የሆነው፥ ሰው ፈጣሪውን ተረድቶና ረክቶ ፍለጋውን እስካቆመ ድረስ፥ ብዙ ነገሮችን እያመለከና ስለነሱም እየተናገረ ያለፋቸው ብዙ ታሪኮችና መላምቶች ስላሉ፥ ነገረ መለኮቱን ከነሱ ለማራቅ ነው::

Dr.Jean Baker Miller የሚባሉ "For human beings it is absolutely true that life is not only biological, it is also psychological and intellectual. The mind is constantly pushing toward growth. It cannot stand still, nor can it really go backward to some earlier level of organization." እንዳሉት፥ ማለትም:- ለሰው ልጅ ሕይወት በሚዳሰሰውና በሚጨበጠው አካሉ ብቻ የሚወሰን አይደለም:: ከሚዳሰሰው አካሉ ቁጥጥር ውጭ በሚያስበውና ለማወቅ በሚያደርገው ጥረቱ ጭምር ነው:: የማወቅ ኃይሉ ያለማቋረጥ ከእውቀት ወደ እውቀት ይገፋዋል:: በአንድ ቦታ እንደ ማይነቃነቅ ሐውልት የተገተረ አይደለም:: አስቀድሞ የጀመረውን እያሻሻለ ወደፊት ከመራመድ በቀር፥ አስቀድሞ ወደ ጀመረው ተግባረ-እዱ ወደኋላ አይመለስም:: እኒህ የዘመኑ ምሑር የተናገሩትን፥ ከቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አባቶቻችን አንዱ መምሕር ገብረ ሥላሴ የተባሉ የወሊጋው ተወላጅ ኢትዮጵያዊው ሊቅ በሚከተለው ቅኔያቸው አስቀድመው እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል::

"ኢየኀድር ግብር: ዘእንበለ ተስፋ፥ ዕፅኒ ይቡስ: የኀድር በተስፋሁ::
አኮኑ ይፈሪ: ድኅረ ተቀስመ ፍሬሁ::
ወቦሙ ተስፋ: ለማያት ዘብዝኁ::
እንዘ በተጽናሶሙ ይጸንሁ: እስከ አመ ይግብእ ፍትሕ: ምልዐተ ማያት በዕድሜሁ::
ሰብሰ እንበለ ተስፋ: አስተኀለፈ ግዜሁ::
በክረምት ወበሐጋይ: እስመ ኢይዐርፍ ሕሊናሁ::
ወየዐርሮ ካልዕ :ለእንተ ዘርዐ ለሊሁ::
ለንባበ ወንጌል ቀዳማዊ: እስመ ዮም ትርጓሜሁ::

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የማይለዋወጠውን ነገረ መለኮት፥ በሰባዊ አዕምሮና ጥበብ እየተለዋወጠና እየገሰገሰ ከሚጓዘው ባሕሉ (ተግባሩ) ለይቶ ይጠብቅ ዘንድ፥ ፈጣሪ "ዕቀብ" ብሎ አዘዘው:: በተቃራኒው ደግሞ ሣሩን፥ ቅጠሉን፥ አፈሩንና አካባቢውን እያፈረሰና እየናደ፥ ቅርጻቸውንና ይዘታቸውን እየለዋወጠ በመጠቀም፥ በመሬት ላይ መኖር ይችል ዘንድ "ተገበር" ብሎ አዘዘው:: አባቶች ከላይ የተዘረዘሩትን መጻሕፍት በነዚህ ታላላቅ ርዕሶች በ"ተገበር" ና በ"ዕቀብ" ከፍለው ይተረጉሟቸዋል:: አሁን አብጅ (ተገበር) የምትለዋን ርእስ ከብሉያቱ እስከ ሊቃውንቱ ባሉት መጻሕፍት እንዴት እንደሚአብራሯት እንመለከታለን::

# ክፍል ፩. "አብጅ"

"አብጅ" የምተለዋ አምላካዊ ቃል (ትእዛዝ)፥ የሰው ልጅ ለቁሳዊ አካሉ ይጠቅመው ዘንድ አካባቢውን እያፈረሰና እየለዋወጠ የመኖር ብሂሉን (ባህሉን) የምትጠቁም ቃል ናት:: ይህን ለማብራራት አባቶች የሰውን የማበጀት ተፈጥሯዊ ባሕርይ ለመግለጽ የታዘዘባቸውን ሁለት

አረፍተ ነገሮች በአንቀፅት ማለትም በብሉያትና በሐዲሳት (First sources) ግንዛቤ ለመግለጽ እሞክራለሁ:: ከብሉይ ኪዳን ልጀምር::

## ሀ. አብጅ፥ በብሉይ ኪዳን፥

፩ኛ "ተባዝኁ፥ ምልዕዋ፥ ቅንይዋ ለምድር" (፩:፳፰)

፪ኛ "ወነሥኦ እግዚአብሔር ለአዳለ እመሕያው ዘገብሮ ወሤሞ ውስተ ገነት ከመ ይትገበራ ወይዕቀባ: (ዘፍ ፪:፲፭):: የሚለውን በአንድ ወገን አድርገው "አብጅ" በምትለዋ አምላካዊ ቃል አጠቃለው እንዲህ ይተሩሚታል::

በመጀመሪያ ፈጣሪ ሰውን ከፈጠረ በኋላ ይጠብቃት እና ያበጃት ዘንድ በገነት ሰየመው:: "ጠብቅ" የምትለዋን ቃል አውጥተን የቀረውን አረፍተ ነገር ስንመለከት "ያበጃት ዘንድ ሰየመው" የሚለው ሐረግ ተባዝሑ፥ ምልዕዋና ቅንይዋ ከሚሉት ትእዛዝ ይዛመዳል:: አዳም በገነት ሲኖር "አብጅ" ተብሎ የተሰጠውን ጸጋ ይዞ ወደ መሬ መጣ:: በመሬት ላይ "ተባዛ፥ ምላ፥ ግዛ፥ ድከም፥ ጣር፥ ጋር፥ ሙት" ተብሎ ከተነገረው ጋራ ተቀላቅሎ የሰው ባህርይ ሆነ:: "አብጅ" በምትለው ቃል አማካይነት ለሰው የተሰጠው ትእዛዝ፥ በመሬት ላይ ለመባዛት ከሚፈጽመው ከንውን ጀምሮ የእለት ምግቡን ለማግኘት እከሚያደርገው ጥረት ድረስ፥ የፈጣሪውን ረድኤት ድጋፍ አድርጎ የሚአከናውነውን አስተዋጽኦ ሁሉ የምትጠቁም ነው::

ሰው ለመኖር መብል፥ ልበስና ቤት ያስፈለጉታል:: እነዚህን ሁሉ የሚያገኘው ከራሱ በፊት በተፈጠረችው መሬት እንዲበቅሉ የታዘዙትን ነገሮች፥ ለራሱ በሚመቸው መልክ በማበጀት ነው:: በአሪቱ ዘመን የመገናኛውን ድንኳን የሰሩት እነ ኤልያብ ከዚያ በፊት ሰው ተጠቅሞበት የማያውቅ፥ አዲስ የማበጀት ክዋኔ፥ የኪነት ምንጭ ከሆነው አምላክ በመቀበላቸው፥ "ጠቢባነ ልብ"(ዘጸ ፴፮:፩) ተባሉ:: በዘመኑ የነበሩ ሴቶችም "ወኩሎን አንስት እለ ሐለያ በልቦን ወበጥበብ ፈተላሁ ለጸጉረ ጠሊ" (ዘጸ ፴፭: ፳፮):: አምላክ የሚመለክበትን ንዋያት ለማሟላት ያቀረቡት የተደነቁበት የእጅ ፈትላቸው ነበር::

መክብብ ሰው በልቶና ጠጥቶ ደስ እንደሚለው ሁሉ፥ በድካሙም የሚያገኘው ደስታ ጸጋ ነው (መክ ፫:፲፫) አለ:: ዕዝራ ሱቱኤም "በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች በዚህ ዓለም የሚደረገውን ምሥጢር ማወቅ ይችላሉ"( ፪:፳፩) ብሏል:: የኢትዮጵያን ስነ ጽሐፍ ጀመረ የሚባለው ሄኖክም "በዚህ ዓለም ለሚኖሩ ፍቅርንና የቀና ነገርን ለሚሠሩ ለኋላ ልጆች ሁሉ፥ ጥበብና ትምህርት ትድረስ" አለ ( ሄኖ ፴፩:፲፫):: ለነኤልያብ፥ ለነ ሄኖክና ዕዝራ ሱቱኤል የተገለጸው ተኬንዎት መልኩ፥ መጠኑና ስፋቱ አድጎ በቤተ መቅደስ ሳይወሰን፥ በየቤታችን ገብቶ ለምንተኛበት አልጋና ለምንቀመጥበት ወንበር ሁሉ ምንጭ ሊሆን ችሏል::

## ለ. አብጅ፥ በሐዲስ ኪዳን

ጌታችን ክርስቶስን ያሳደገው ቅዱስ ዮሴፍ፥ የዘመኑን ተኬንዎት በመጠቀም በሚአበጀው ይተዳደር ነበረና፥ ክርስቶስ "የጠራቢ ልጅ" (ማቴ ፲፫:፶፭) በመባል ተነቅፎበታል:: "ይህ ሥጋየ ነው" (ማቴ ፳፮:፳፮-፳፰) ብሎ የሰጠን ሥጋውና ደሙ፥ የሰው ልጅ በዘመኑ ባሕል ከሰንዴና ከዘቢብ ያዘጋጃቸው ምግብና መጠጥ ናቸው:: በተለየ መንገድ ሠርታችሁ አምጡልኝ አላለም:: ዘመኑ አበጅቶ ያቀረበውንም ታንኳ ለመጓጓዣ ተጠቅሟል:: "(ማቴ ፲፩: ፲፫):: የሆሳዕናዋ አህያም ባሕሉ የገራትና ያሰራት እንጅ፥ የሰው ልጅ ያልተጠቀማባት የሜዳ አልነበረችም (ማቴዎስ ፳፩:፪):: ታላቁ አንጋፋ መምሕር ቅዱስ ጳውሎስም፥ ይተዳደር የነበረ በሚአበጀው ድንኳን ነበረ (የሐዋ ፲፰:፫):: ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ ራስን ከእግዚአብሔር ፈቃድ አለማራቅ ዘለቄታ ጥቅም እንዳለው በገለጸው አንቀጽ፥ ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድም ይጠቅማል ሲል፥ አብጅ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ እንዳይረሳ መክሮታል (፩ኛ ጢሞ ምዕ ፬: ፰)::

# ክፍል ፪. "አብጅ" በመጽሐፈ ሊቃውንት

መጻሕፍተ ሊቃውንት (ሃይማኖተ አበው) ከብሉዩና ከሐዲሳቱ መጽሐፍ መንጭቶ እኛ ዘንድ ደርሶ ከኛም አልፎ የሚቀጥል ስለሆነ ፈለግ (Second resources) ይባላል:: ይህ መጽሐፍ የፈጣሪን ተኬንዎት በብዙ ቦታ የማይተረጎም ይለዋል:: "ነአምን ከመ ቃል ኀደረ ውስቴታ እምኔሃ ፍጡነ ከመ ቅጽበተ ዐይን በዘኢይይተረጎም ወዘከመ ለሊሁ የአምር ውስተ ከርሰ ድንግል: ወኢተፈልጠ ተዋሕዶተ መለኮት ዘኢይትከፈል በትስብእቱ ለዋሕድ::"(ሃይ ፺፮:፲፪-፲፫) ማለትም:- አምላክ የሰው ልጅ ያድን ዘንድ በረቀቀ አምላካዊ ተኬንዎቱ ያለወንድ ዘር በእመቤታችን ማሕጸን ከረቂቁን መለኮት ከሰውነቱ ጋራ አዋሐደው (አበጀው):: ፈጣሪ ለፈጠረውና ላበጀው ሁሉ ሰው የመጨረሻውና መደምደሚያ ነው:: ፈጣሪ ሌላውን ከፈጠረበት ሁሉ ተኬንዎቱ፥ ሰውን ያበጀበትና ያዳነበት ተኬንዎቱ እጅግ የረቀቀ ነው ይላሉ አባቶች:: ሰው ራሱን አጥንቶ ለጥናት አስቸጋሪ መሆኑን የተረዳው አሁን በቅርቡ ነው:: አሁንም ቢሆን ሰው ራሱን ያወቀው በመጠኑ ነው::

አባቶቻችን በዚህ ግንዛቤ አምላክን ለማመስገን ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ፥ ብራና ፍቀው፥ ቀለም በጥብጠው፥ ብዕር ቀርጸው የጻፉትን ከማር ሰፈፍ ባበጁት ጧፍ አማካይነት የማይጨበጠውን እሳት ጨብጠው "ዘአንሣእከነ እምድር ወአልዐልከነ እመሬት ከመ ታንብረነ ምስለ መላእክቲከ ወምስለ መላእክተ ሕዝብከ"( ፱:፳፩) እያሉ ነው:: ይህም ማለት "እኛን ከመሬት ቀምመህ የሰራህ፥ እንደገና ወደ መሬት በመመለስ የምታፈርሰን፥ እንደገና አፈር ትቢያ የሆነውን ሰውነታችንን እንደገና ከመሬት አንስተህ አበጅተህ ባዘጋጀህልን ከተማ በክብር እንድንሮር የምታደርገን ፈጣሪያችን ሆይ! እያሉ አምልኮታቸውን የሚገልጹት "ወኬንያ ፍጥረትነ" በማለት፥ የራሳቸው ሰውነት በማንበብ ነው:: የራሳቸውን ሰባዊ ተፈጥሮ የተኬንወቱ መግለጫ፥ የአምልኮታቸው መሠረት አድርገው ይጠቀሙበታል::

ሠለስቱ ምዕት "አኮ ከመ ብዕሲ ዘጻመወ ወአዕረፈ: አላ ሰይፈ እሳት ይውጽዕ እምአፉሁ ዘነበበ በጊዜሃ ይገብሮ ወዘሀለየ በቅጽበት ይከውኖ ዘውእቱ ሕሊናት ጠቢብ ወኬንያ::"( ገጽ ፻፺፬: ቁጥ ፳፰) እንዳሉት: ማለትም:-እንደሰው ደክሞት አያርፍም:: ነገር ግን ይሁን ብሎ ፍጥረቱን የሚያከናውንበት ቃሉ ቅርጽና ይዘት የሚሰጥ እሳት ነው:: የተናገረውን ራሱ ባቀደው ሰዓት ይፈጽማል:: በአሰበባት ቅጽበትም ያከናውነዋል:: እርሱ የማይመረመር የረቀቀ ሐሳብ ነው:: እራሱ የጥበብና የክንውን መሠረት ነው" እያሉ ሊቃውንት አበው በቤተ ክርስቲያናችን አምልኮታቸውን ሲገልጹ ኖረዋል::

"ኦ አምላክ ዘለዓለም ቀዳሚ ወደኀሪ ዘአልብከ ጥንት ወኢተፍጻሚ:: ዘዐቢይ በተኬንወቱ ወኃያል በምግባሩ ወጠቢብ በምክሩ ወጽኑዕ በኃይሉ:: ዘሀልው ውስተ ኩሉ ምስለ ኩሉ::"(ቅዳሴ ገጽ ፵፯ ቁጥ ፲፰) ማለትም:- ጥንትና ፍጻሜ የሌለህ ተኬንዎትህ ረቂቅ ኃያል (almighty) ጥበብህና ሥራህ ምጡቅ (omniscience): ምክርህ የማይለወጥ በሁሉ ውስጥና ከሁሉ ጋር ያለህ (omnipresence) እያልን በየእለቱ እንድንቀድስበት የተዘጋጀው መጽሐፈ-ቅዳሴያችን፥ ሰባዊ ባሕል ለወለደው ቴክኖሎጂ የሚሰጠው ክብር ከፍ ያለ ነው:: ከቁሳዊ አካል ውጭ ለሆነው ረቂቅ መለኮታዊ ቴክኖሎጅ፥ የሰው ልጅ የሚያበጀውን ማስረጃ በማድረግ የአምልኮታችን ሥርአት ተቀየሰ::

የግዕዙ ሊቃውንት ለሚአበጁት ጁሉ "ተኬነወ" የሚል መግለጫ ግሥ ፈጥረውለታል:: ትርጉሙ ብልሐተኛ ሆነ ማለት ነው:: በውጩ ቋንቋም technique የሚባለው ቃል እንዳለ ሆኖ " The way in which the fundamentals, as of an artistic work, are handled" ተብሎ እየተሰበከ የዓለማችንን ባሕልና የኑሮ ዘይቤ እየለወጠው መጥቷል:: ይህንንም አባባል "ጸጉ አእምሮ ለአዕይንተ አልባቢነ ወዕቀብ ከናፍሪነ እምነነገር እኩይ፥ ሰላመ ኀበነ ወጽድቀ መሐረነ እስመ አንተ ልብስነ ወፈውሰ ሕማምነ ወኬንያ ፍጥረትነ::(ቅዳሴ ፲፩: ፴፬) ማለትም:- "አፋችንን ከክፉ ነገር ጠብቅ ሰላም ስጠን፥ ይቅር በለን፥ ልብሳችን ነህ፥ ሐኪማችን ነህ፥ የተፈጥሯችን ምንጭ (ኬንያ) ነህ" እያሉ

ከራሳቸው ተፈጥሯዊ ቅንብር ጋር በማገናዘብ፥ አባቶች ከሞራልና ከጠቅላላ ስነ ባህርይ ጋር ቴክኖሎጅን እያዋሐዱ አስቀድመው ገልጸውታል::

technique የሚለው ቃል ቅጽልና ስም እያመነጨ technology ከሚለው አፋፍ ላይ በመድረስ ዓለምን ካለችበት ደረጃ ላይ ላደረሳት ጥበብ የተሰጠ ስም ነው:: ቀደም ብሎ የተዘጋጀው መጽሐፈ ቅዳሴአችንም "ኬንያ" የሚለው ቃል "ተኬነወ" ከሚለው ግሥ ተነሥቶ "ኪነት" የሚለውን ሳቢ ዘርና "ኬንያ" የሚለውን ባእድ ዘር እንደሚወልድ አርገው የቴክኖሎጂ ምንጭ የሆነውን አምላክ ቴክኖሎጂውን እያነሳሱ በቅዳሴያቸው ሲያወድሱበት ኖረዋል፥ ለእኛም አውርሰውናል::

በአንዲት ቅድስት ተዋሕዶ እምነት ተሰባስበው ለሚያሚልኩት ወገኖች "ያብእክሙ ኀበ ተተክሉ ደባትር ዘነደ እሳት ኀበ ሀሎ ሊቀ ካህናት ሀየ ሀሎ መልክአ ገጹ ሥዐል አክሊል ንጹሕ ወአልባስ ብሩህ ዘኢተኬነዎ እደ እጓለ እመሕያው አላ ዘእምላእሉ እንመቱ:(ቅ ማር ገጽ ፪፻፲፮:ቁጥ ፪፻፶፰) ይላሉ:: መለትም:- "ሊቀካህናት ኢየሱስ ባለበት ንጹህ አክሊልና ከምድራዊ ጥበብ አሠራር በላቀና በረቀቀ ጥበብ የተሠራ ንጹሕ ልብስና አክሊል ወዳለበት ያግባችሁ::" ይህ አባባል አስደናቂው ሰብአዊ ቴክኖሎጂ የሚያመነጨው ሁሉ ምድራዊ ጥበብ በመለኮታዊ ጥበብ ለተሰራችው ሰማያዊት አዳራሽ መግለጫና፥ በውስጧ ለመኖር እንድንጓጓ የሚደርገን ነው::

Technologies for creating ለሚባለው ትምህት መሪና አስተማሪ የሆኑት Robert Fritz የተባሉ ሊቅ "Learning to Become the creative Force in your own life" በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፋቸው እንዲህ አሉ::

"There is a profound lesson here. It is partly about the human spirit. We have been led to believe that the circumstances of our life determine our ability to express ourselves that for us to explore new dimensions of our being, our conditions need to be favorable. If that were true, how could such creativity, originality, and vitality come from such humble and adverse beginnings as the ghetto? How is it that it was from there, and not the sacred institutions of academia, that new thought, born of what is hghest in humanity, developed and grew? Perhaps our true nature is that of creators, who can bring new life out of any set of circumstances."(48) ይህ አባባል የሃይማኖታችን መጽሐፍ አብጻት ስለምትለው መለኮታዊ ስጦታና፥ ሰባዊ ባሕርያችን የሚያብራራ ሲሆን፥ ከነዚህ ሊቃውንት በፊት፥ የኛ አባቶች ከላይ እንዳልነው በትርጌሚያቸውና በጸሎተ ቅዳሴያቸው ግልጸውታል::

መመሪያችን ፍትሐ ነገሥቱ በገዳም ተወስነው ስለሚኖሩት መነኮሳት እንኳ ሲናገር "መምህራንኒ ይፈቅዱ ከመ ይኩኑ አርዳኢሆሙ ሠናያነ አዕምሮ ወምግባር: ውስተ ኪነታቶሙ: ወይኩኑ ተመሃርያነ ትሩፋነ ወመዋዕያነ ለዘይትቃወሞሙ: ወበእንቲአሆሙ ይትአኮቱ መምህሪኒሆሙ እስመ ዝንቱ ጽድቅ ይበጽህ በፍጻሜ ተልእኮቶሙ:: (አንቀጸ መነኮሳት ፲: ቁጥር ፫፻፳፩ ገጽ ፪፱) ብሏል:: ማለትም:-በገደማቸው ተወስነው በተግባረ ዕዳቸው የሚራቀቁ፥ በተደሞና በአርምሞ ግርማ በተጎናጸፈው ተግባረ-እዳቸው እረድኤት አካባቢያቸውን ለመለወጥ የመጠቁ፥ በዚህ ተግባራቸውና ተልእኳቸውም መምህሮቻቸውን የሚአስመሰግኑ" እንዲሆኑ አጥብቆ አደራ ይላል::

በዚህ ተማኅጽኖ "አብጅ" የምትለዋ ለመነኮሳት የተሰነዘረችው ትዕዛዝ፥ ምንኩስና የጸሎትና የተፈጥሮ ምርምር ተማሪነት መሆኑን የምትጠቁም ናት ይላሉ አባቶች፥: ከዩኒቨርስቲው ወጥቶ በቀለጠው ከተማ የሚኖር ተማሪ፥ ፈተናውን አልፎ ከዲግሪ ማእረግ ሊደርስ ቀርቶ፥ የተማሪነት ባሕርይ እንደማይኖረው ሁሉ፥ ከገዳሙ ወጥቶ በቀለጠው ከተማ ከሕዝብ ጋራ እየተጋፋ የሚኖር መነኩሴም፥ ስንኳን ለሌላው በሚያበጀው ተግባረ-እዱ መምህርና ምሳሌ ሊሆን የምንኩስናውን ባሕርይ ያጣል:: ሰው ነውና፥ ተፈጥሮን መካድ አይቻልምና "ጸልይ" እና "አብጂ" ከሚለው ክልል መንፈሱ ይወጣል:: ከገዳሙ የወጣ መነኩሴ ከባሕሩ ከወጣ ማየትና መተንፈስ የማይችል አሳ ነው:: ከባህሩ የወጣ አሳ ከሚበሩ አእዋፍና በደረታቸው ከሚሳቡ ነፍሳት ጋራ ቋንቋና ሕይወት እንደሌለው ሁሉ፥ መነኮሳትም የመአስባንን ኑሮ ስለማያውቁትና ስለማያስቡት፥ ስለትዳር፥ ስለልጅ ማሳደግና ኑሮ ለማስተማር መሞኮር መሳሳት ነው::

ቅዱስ ጳውሎስ "በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው እነዚህ ውሸተኞች መጋባት ይከለክላሉ"( ፩ኛ ጢሞ ፬:፫) ሲል በምሬት የተናገረው፥ ምንኩስናን ለመቃወም አይደለም:: እነ እንጦንስ ምንኩስናን ለምን እንዳበጁት ሳይረዱ ከገቡበት በኋላ፥ የምንኩስናውን እንቅስቃሴና ባሕርዩን ገልብጠው ወደመተዳደሪያነት ለውጠው ስለሚአበጁት ምንኩስና ነው:: የዚህ አይነት መኮሳት፥ የሌሉበትን ዓለም ሕልም የሚአወሩ ይሆናሉ:: በመጨረሻም "መላክ ነበርኩ: ሰው ሆንኩ" በሚለው ስሜት ይያዙና፥ ሕቡዕ የሆነ ዓለማዊ ሕይወት ያበጃሉ:: ቆባቸውን እየቀደዱ መስፋት ይጀምራሉ:: "ሥራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል" የሚለው በከንቱ የመጣ አይደለም:: ምንኩስና እንዲአበጅ የቆመበትን ሳተ ማለት ነው:: ይህ በኦርቶዶክስ ስርአተ ምንኩስና ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም:: ምንኩስና አልፎ አልፎ በተለያዩ ዘመናት በታላላቅ ከተማ ብቅ እያለ አንዳንድ ስሕተቶች ሲፈጥር ቢታይም፥ ከገዳም ወጥቶ መተዳደሪያ እንዲሆን ያበጁት አቡነ ጳውሎስ ናቸው::

ሰው በማይኖርበት ዓለም ውስጥ ምንም ማበጀት አይችልም:: ጠቢባኖች ሰው የሚኖርባትን ዓለም እንዲያበጃት ፈጣሪ የሰጠውን ጸጋና ችሎታ ከካደ ከእምነት ጋር የሚጋጭ መሆኑንን እንዲህ እያሉ ይገልጻሉ:: “The only way to proceed to the future is through the appropriation, the continual re-appropriation, of tradition. The goal of the interpretive approach to the human world is to cultivate such habits, to recognize that we are condemned to remain open, both to the past and to the future. (20) ” ማለትም:- ወደፊት በእድገት ጎዳና ለመቀጠል በተገቢው ባህላዊ መንገድ እንደገና መንቀሳቀስ ነው:: ሰብአዊ ኃላፊነት፥ ትርጉም ባለው አቀራረብ ዓለምን መቅረብ ነው:: ባለፈው ዘመን ለተከሰተውና ወደፊት ለሚከሰተው ነገር አዕምሮን ክፍት አድርጎ መኖርን መቀበል ነው::

ለኑሯችን ይመቸን ዘንድ ያለውንና የነበረውን ቅርጽና ይዘቱን እየቀያየርን የምንሰራው ነገር ማበጀት እንጅ መፍጠር አይደለም:: አምላክ በገነትም በመሬትም ለሰው ልጅ የሰጠው ጸጋ ነው:: በገነት የነበረውን ሕይወት በፈቃዱ ቀይሮ ከገነት ከወጣ በኋላ "በተግባርከ ወበጻእርከ ብላዕ ኩሎ መዋእለ ሕይወትከ: አሥዋከ ወአሜከላ ይብቁልከ: ወብላዕ ሣእረ ገዳም:: ወበሐፈ ገጽከ ብላዕ ኀብስተከ እስከ ትገብዕ ውስተ መሬት እንተ እምኔሃ ወጻእከ"(፫:፲፯-፲፱):: ማለለትም:-መሬት ነህና ወደ መሬትነትህ እስክ ትመለስ ድረስ፥ እስኪያልብህ እየሠራህ፥ ከእሾህ ከአሚከላ ጋራ በመታገል እያበጀህ ኑር! ተብሎ በፈጠረው አምላኩ ታዘዘ::

እነዚህ እሾህና አሚከላ የተባሉት፥ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ግንዛቤ ለተሐዋስያን (bugs, germs, virus) የተሰጡ "ሰማሰም" ስሞች ናቸው:: እነዚህ እሾሆችና አሚከላዎች አብጅ በሚለው ትእዛዝ ከተሰማሩት የሳይንስ ሊቃውንት ጋራ ትንቅንቅ ላይ ነው ያሉት:: በቢሊዮን የሚቆጠሩ በአይናችን የማናያቸው ተሐዋስያን ሊቃውንት አበው "በነፋስ፥ በጢስ፥ ይትሜሰሉ ይመጽኡ" እያሉ የሚተረጉሟቸው ናቸው:: ከነዚህ ተሐዋስያን ጋራ የሚታገሉት የዓለም ልጆች እነዚህን ሁሉ ረቂቃን ጣላቶች ለማሸነፍ በሚያደረጉት ጥረት አፈ ታሪኩን፥ ባሕሉን፥ ቅሬቱን፥ ያለፈውን፥ ያለውን፥ የሚታየውንና የማይታየውን ገደሉንና ተራራውን እየቧጠጡ ናቸው::

እሾሕና አሜከላ የተባሉት እነዚህ ተሐዋስያን ለመታገል፥ ሰው በማበጀት ክሂሎቱ መከላከያ ቢአበጅም፥ ይህች ምድር እየታገልን የምንቆይባት የጦር ሜዳ ናትና ማበጀቱ ይቀጥል ዘንድ፥ ተሐዋስያንም ሰውን የሚታገሉበትን መንገድ ይለዋውጣሉ:: ሰይጣን የታመመውን በሽተኛ "ጳውሎስን አውቃለሁ፥ ኢየሱስንም አውቃለሁ ኸረ አንተ ማነህ? አለ ብሎ ቅዱስ መጽሀፍ እንደሚነግረን፥ የሰው ጣላቶች ተሐዋስያንም ቅርጻቸውንና ባሕርያቸውን በመለዋወጥ "መድኃኒቱን አውቀዋለሁ፥ ዶክተሩንም አውቀዋለሁ አንተ ማነህ? እያሉ ናቸው::

የተፈጥሮ ሳይንስ ሊቅ ዶር ቨራረነ የተባሉ ሊቅ በሰውና በተሐዋስያን መካከል ያለውን ትግል ለመግለጽ የተናገሩትን እጠቅሳለሁ:: “The bugs say, “We don’t care what type of drugs you put on us. We’ll just mute-because there’s one thing about us insect; we don’t care about being’ ugly. We don’t take long time to mutinize we don’t care how we look. We just get the job done.”( 59) ማለትም:-እኛን ለማጥፋት

የፈለከውን አይነት መርዝ ርጭብን:: ምንም አይጨንቀንም:: የምትነሰንስብን መርዝ ለመቋቋም በምናደርገው ትግል ቅርጻችንን ለውጠን ለመምጣት ሩቅ ጊዜ አይጠይቀንም:: ሥራችንን አናቆምም:: እንደገና እንቀጥላለን ይላሉ ብለዋል::" ሊቁ የተነገሩት ይህ የተሐዋስያን መፈክር "ርግምተ ትኩን ምድር በተግባርከ ወበጻእር ብላዕ ኩሎ መዋዕለ ሕይወትከ:: አሥዋከ ወአሜከላ ይብቁልከ ወብላዕ ሣእረ ገዳም:: ወበሐፈ ገጽከ ብላዕ ኅብስተከ" (ዘፍ ፫:፲፯) የሚለውን ቃል ይተረጉማል:: በገነት የነበረው የማበጀትና የመጠበቅ መልክ ተለወጠ:: የገነቱ ኑሮ የመዝናናት፥ የደስታ፥ የሰላም፥ የጤና የክብር ነበር:: መሬት ግን እሾሑን አሜከላውን በማብቀል፥ ሙቀቱንና ቅዝቃዜውን በማመንጨት የማትመቸው የጦርነትና የትግል መቆያ ሆነች:: ይህንንም አበባል ቄርሎስ የተባለው ሊቅ "በኃጢአት ዓባይ እንተ ጸንአት ላዕሌነ ጥቀ በእንተ ፈቃድነ እንተ ወፅአት እምሕላዌሃ እንተ ይእቲ ጥንተ ኃጢአት. . . ."(ሃይ አበው ምዕ ፸:፲፱) በማለት ገለጸው::

በገነቱ ኑሮ ውስጥ ከሰው ልጅ ይጠበቅበት የነበረው የማበጀትና የመጠበቅ የደስታና የሐሴት አስተዋጽኦ ብቻ ነበር:: ወደ መሬት ሲመጣ ሰውነትን የሚያስጨንቅ ልማትና ጥፋት፥ ሳቅና ልቅሶ፥ ጤንነትና በሽታ ሕይወትና ሞት የተቀላቀለበት የሕይወት ሸክም ወደቀበት:: "ምንም መርገም የሌለባት የእዚአብሔር ዙፋን የተዘረጋባት፥ ክርስቶስ ነግሶ ሲመለክ የሚኖርባት" (ራዕ ፳፪:፫-፭) በጸሎታችን "ትምጻእ" የምንላት ሰማያዊቷ ከተማ እስክትረከበን ድረስ ጣሩ ይቀጥላል:: እንግዲህ የክርስትናችን መጻሕፍት ተስማምተው እንደሚገልጹት፥ የሰውን አስተዋጽኦና ተኬንዎት (ማበጀት) የማትጠይቀው ይህች በሰማይ ያለችው ከተማ ብቻ ናት::

"ብነ ሕንጻ በኀበ እግዚአብሔር በሰማያት ዘኢ*ገ*ብሮ እደ ሰብዕ" (፪ኛ ቆሮ ፭:፩) ማለትም:- ስምሕን ለሚወዱ ሰዎች በሕሊናቸው ሊገምቷት በጆሯቸው ሊሰሟት ከሚችሉት ውጭ የሆነችውን ቦታ ያዘጋጀህ አምላክ ሆይ!" እያለ ቅዱስ ጳውሎስ ይህችን ከተማ ገልጿታል:: ሊቃውንት አበውም ከሐዋርያት ተቀብለው "ኦ እግዚኦ ዘዓይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰማዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢትህለየ ዘአስተዳሎከ አምላክ ለእለ ያፈቅሩ ስመከ" (ቅዳሴ ዮሐ ገጽ ፫፻፲ ቁጥ ፴፮) (ሃይ ማኖተ አበው ምዕ ፰፭: ፴፭):: እያሉ ገለጿት:: እነዚህ ሁሉ ሊቃውንት መንፈሳውያን አባቶች በመለኮታዊ ቴክኖሎጂ የተሰራችውን ከተማ ለማድነቅ የተባበሩት "ጸሐይዋ ጨረቃዋ እግዚአብሔር፥ መብራቷ ክርስቶስ፥ ሌትና ቀን የሌለባት የእግዚአብሔር እጅ የሚጠብቃትና የሚያበጃት እንደሆነች ዮሐንስ በራዕይ የገለጻትን ናት:: ክርስቶስም "አስቀድማ የተዘጋጀች" (ማቴ ፳፭:፴፬) ናት ብሏታል::

"አምላከ ብርሃን ወላዴ ሕይወት ርእሱ ለአዕምሮ ወሀቤ ጸጋ ዘእምጸጋ ፍጹም. . . . መዝገበ ጥበብ ረዳኢ መምህረ ቅዱሳን ወመሠረተ ዓለም" (ኪዳን ዘመን ፈቀ ሌሊት) ማለትም ሕይወትን የፈጠርክ የጥበብ መገኛ የውቀት ሁሉ ምንጭ፥ ዘላለም ከማይጎለው ምልአተ ጥበብህ የምታድል፥ የጥበብ ሁሉ መዝገብ፥ የመምሕራን ረዳት፥ የዓለም(የትውልድ ሁሉ) መሠረት የሆንክ አምላክ" እያልን የምናመሰግነው ክርስቶስ ባዘጋጃት ከተማ እስክንገባ ድረስ የማበጀቱ ክንውን ይቀጥላል::

በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች፥ እኛ ዛሬ በዚህች ምድር ላይ የምንኖረውን የኑሮ ዘይቤ፥ ከአንድ ሽህ ዓመት በፊት በዚህች ምድር ላይ ይኖሩ ከነበሩት የኑሮ ዘይቤ ጋራ ብናነጻጽረው፥ በብዙ ክንዋኔዎች ይለያያል:: የዛሬው ኑሯችንም ከመቶ ዓመት በኋላ ከሚኖሩት ትውልዶቻችን ክንዋኔ ጋራ ሲነጻጸር፥ ፈጽሞ የሚገናኝ አይሆንም:: ይህ ባዝጋሚና በፈጣን እንቅስቃሴው የሚጓዘው ሰባዊ የማበጀት ኑሮ፥ ጸረ-ሕዝብና ፍቁረ-ሕዝብ ለሆኑትን መሪዎች መመዘኛ ሚዛን ሆኗል::

ለምሳሌ:- ከራሳቸው ምቾት የሕዝቡን ምቾት የሚያስቀድሙ እንደ አጼ ምንይልክና አጼ ቴዎድሮስ ያሉ የቤተ ክርስቲያናቸውን መጽሐፈ-ቅዳሴ የተረዱ ብሩህ አዕምሮ የነበራቸው መሪዎች፥ በዘመናቸው ብልጭ ብላ የታየቻቸውን የቴክኖሎጂ ጭላንጭል ከውጭ አምጥተው ለሕዝባቸው ለማጉረስ በመጓጓታቸው ካልተረዱላቸው መንፈሰ-ጣዖታት ካህናት ጋራ እንደተጋጨ ሁሉ፥ በተቃራኒው ደግሞ፥ ሕዝቡ በዓለም የሚታየውን የቴክኖሎጂ ወገጋን አስቀድሞ አይቶ ወደ ቤቱ ለማስገባት ሲታገል የሚያዳፍንበት መሪና ተባባሪ መጽሐፈ ቅዳሴያችንን ያልተረዳ ፓትርያርክም ተፈጥሯል:: ይህም ማለት በኅብረተ ሰባቸው መርዝ የሚረጩ ከሰውነት ወደ (bugs, germs, vires)

ነት የተለወጡ ናቸው ማለት ነው::

ድኀ ቅኔና ያንድምታው ትምህርት ብቅ ባሉበት ዘመን፥ ላለመቀበል የታገሉ ሰዎች እንደነበሩ ሁሉ፥ በአጼ ምንይልክ ዘመን "አብዳት" የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ያልተገነዘቡ ሰዎች የስልክን አገልግሎት ለመቀበል ችግር እንደነበረባቸው ከቅርብ ታሪካችን የምንረዳው ነው:: ታዲያ ዛሬ እንደምንሰማው የእጅ ስልክ ያልገባበት ቤት የለም:: የሚያሳዝነው "አብጅ" የሚለውን ተኬንወት (ክሂሎት) ጠብቀው የሚያበረክቱት ቅዱሳን ሰዎች እየደከሙ ሳሉ፥ ማነኛውንም ጠቃሚ ነገር ለሰው ልጅ እኩል እናስተናግዳለን፥ እናሳትፋለን ብለው የመንግሥትነትን ስልጣን ይዘው በአሳላፊነትና በአስተናጋጅነት እራሳቸውን የሰየሙ ሰዎች፥ ይህ የተቀደሰው ቴክኖሎጂ ለማንኛውም ዜጋ እኩል እንዲደርሰው ከመጣር ይልቅ፥ ለማፈንና ለማዳፈን የሚያጠፉት ገንዘብ የሕዝቡ ገንዘብ ስለሆነ፥ በሕዝባቸው ላይ የሚፈጽሙት ደባ እንቅብ-የዕንቅብም-ዕንቅብ (bugs, germs, virus) ያደርጋቸዋል::

ወደ አሜሪካ መጥቼ እጅግ የመጠቀውን የማበጀት ክንውን ስመለከት፥ በጫካና በገደል መካከል ላይ ሆነው ይህችን ዓለም በቅኔ የሚያሽሞነሙኗት መምህሮቼ፥ እነ የኔታ አምዴና አንዳርጌ ከፊቴ ይመጡብኛል:: "ወብርሃንሰ ዘውስተ ጽልመት: ያበርህ ወያርኢ ወጽለመትኒ ኢይረክቦ ወኢይቀርቦ" የሚለውንም፥ በደብረ ሊባኖስ ጫካ በተመሠረተችው ጉባዔው ቤታችን "በሥነ ፍጥረት ተመራምረው ያወቁት እውቀት በስዋሬ ያለ ምሥጢርን ይገልጻል" እያሉ ወዲያ ወዲህ በመካከልን ይንጎራደዱ የነበሩት የኔታ ብርሃኑ ከፊቴ ይመጡብኛል::

"ከመ ይባኡ ውስተ በዓልከ ወይንሥኡ በህየ አክሊለከ ወያእርፉ ውስተ ማኀደሪሆሙ ዘለዓለም በሀገርከ እንተ አንተ ለሊከ ኬንያሃ ወነዳቂሃ:(ቅዳ ፻፶፩: ፸፪) የሚለውንም በትንሽ ጎጇቸው ሆነው አንድም እያሉ ያለፉት እነ የኔታ ፍስሐ፥ እንደኔ እድል ገጥሟቸው በአሜሪካ እየፈሰሰ ያለውን ቴክኖሎጂ መጥተው ቢያዩ መጻሕፍትን እንዴት ይተረጉሟቸው ነበር ይሆን? የሚል ጥያቄ ይፈጠርብኛል:: በገደልና በጫካ ተከበው የማመንጨት ችሎታቸውን አሻግሬ በትዝታየ ስቃኝ፥ የራሴን ደካማነት በሰፊው እንድታዘበው ያደርገኛል:: ቅኔውን እንኳ ሳናውቅ፥ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካህናት ነን ብለን በቤተ መቅደሱ በተሰለፍነው ሁሉ ላይ ሐፍረት ይሰማኛል::

የመነኑ ሰዎች ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ የተናገረውን መመሪያ በማድረግ ጥረታቸውና፥ ጸሎታቸው ከዚህች ዘላለማዊት ቤት ለመግባት ስለሆነ: ቴክኖሎጂው የተስፋቸው መተርጎሚያና ማረጋገጫ ማብራሪያ ነውና ያደንቁታል እንጅ አይቃወሙትም ነበር:: "እሳት አመድን ይወልዳል" እንደሚባለው ባንሆን ኖሮ "ቀቀቀ፥ ከከ፥ የሚል ደጊመ ፊደል እየፈጠርን፥ እርስ በርሳችን ከመጠላለፍ ይልቅ፥ የመረዳት ኃይላችን ለማዳበር ብንታገል፥ ጠቃሚ ነገሮችን የሚአስተምሩ የኦስትሪያው መነኩሴ አባ ጊዮርጊስ የሚባሉት ካመነጨት (ያበጁት) የበለጠ የኛ አባቶች ያመነጯቸው (ያበጇቸው) መጠነ ሰፊ "ዕጸ ደብዳቤዎች" ነበሩን::

ፈጠሪ በገለጸላቸው ተኬንወ ይህችን ዓለም ለመለወጥ የሚጥሩ ሰዎች፥ አዕምሯቸው አዳዲስ ጥበብ ከማመንጨት በቀር፥ ክፉ ነገር ለማሰብ ሰከንድ የላቸውም:: የቀደሙ መንፈውያን አባቶቻችንም በትልቅ አዳራሽ ለመኖር: ክትፎውን ውስኪውን ለመጠጣት ምኞቱ ቀርቶ ሐሳቡ አልነበራቸውም:: የዚህ ዓለም ቴክኖሎጂ ከሚፈጥራት ከተማ እጅግ በበለጠችው ከተማ ገብተው ለዘላለም ለመኖር፥ በስእላቸው በድጉሰታቸውና በቅዳሴው አንድምታ "ወለነሰ ዘውስተ ሰማይ ሀገርነ"(ፊል ፫:፳):: "የእኛስ አገር በሰማይ ነው እያሉ፥ ምድራዊ ሕይወታቸውን አሳለፉ:: የዛሬዎች እኛ ግን በቴክኖሎጂ ውስጥና በጀርባው ያለውን ሕቡዕ አምላክ አሻግረን በማየት እያደነቅን የዚህን ሁሉ ፈጣሪ ከማምለክ ይልቅ፥ በተሸከመው ነገር ሁሉ እንደደፈረሰው አባይ፥ ዓለማዊው እንቅስቃሴ globalization ከጠራው እውቀት ጋራ ቀላቅሎ የሚደልልብን የባህል ቅራሬና አተላ ለመሻማት፥ ቴክኖሎጂውን መሳሪያ አድርገነዋል:: አዕምሯችንንም በእውቀት ከማግዘፍ ይልቅ፥ በዓለም ያለውን ሁሉ ወርቅና ብር ውጠን ሥጋችንን ለማግዘፍ ታጥቀን የተነሣም መስለናል::

ሕዝብን የሚመራ መንግሥትና በዩኒቨርስቲዎች አካባቢ በከተማ የሚኖር ኅብረተ ሰብ

ይቅርና፥ በጫካ የሚኖሩው ሕዝባችን እንኳ የቴክኖሎጂውን ወለላና ዘመራ ጠጥቶ ለመርካት፥ እጅግ የተጠማ ነው:: ከላይ እንዳልኩት፥ ከዓለም ርቀው በገዳም የሚኖሩት መነኮሳትም ቢሆኑ መራቅና መቃወም ያለባቸው ቴክኖሎጂ ተፈናጦ የሚገባውን አሰረ ገሰስ እንጅ የጠራውን ቴክኖሎጂ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያናችን ያከማቻቸውን ቅርስ ከተገነዘብንና አምላካችንን የምንቀድስበት መጽሐፈ ቅዳሴያችንን እንደነ አጤ ምንይልክ ከተረዳን፥ ተክኖሎጂውን ላለመቀበል የጠመመ ፊት ማሳየት የለብንም:: ሰውን በሚጎዳ ሁኔታም ልንጠቀምበትም አይገባም:: ቴክኖሎጂ ሲጠራቀም የኖረው ሰብአዊ ባሕል ያረገዘውና፥ ባሕሉ አምጦ የወለደው፥ ከባሕሉ ስንጥቆ የሚመጣ ስለሆነ፥ ቴክኖሎጂን ለመቋቋም የሚሞክር ሁሉ ተገፍትሮ ከመገልበጥ በቀር፥ ተኬንዎት በፊቱ ያለውን ሁሉ ግርግዳና ጣራ እየሰነጠቀ ለመግባት ያለውን ኃይል ሊቋቋመው የሚችል አይኖርም::

በተለይም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሰዎች የሚጠበቀው ጽላቱን በራሳችን እንደምንሸከመው፥ ቴክኖሎጂውን የተዋሕዶውን ነገረ መለኮት ተሸካሚ ቄስ ለማድረግ መጣር ሲገባን፥ በነገረ መለኮቱ ላይ እየዘመትን፥ ቴክኖሎጂ ለሚሰባብረው ባሕል በምናደርገው ቅጣ ያጣ ጥንቃቄ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከዘመናውያን ምሑራን እየለየናት ነው::

"አብጅ" የምትለው ቃል፥ ሰው በተፈጥሮው የታደለውን ሲመት፥ ክሂሎትና ተኬነወት ያመነጨች አምላካዊት ኃይል ናት:: ይህች ኃይል ሰው ከራሱ በታች ያለውን ተፈጥሮ በሚመቸው መንገድ እየለዋወጠ መጠቀም እንዲችል ለሰው ልጅ የተሰጠች ዛሬ ዓለማችንን በመለወጥ ያለውን ቴክኖሎጂ የወለደች እናት ናት:: ቴክኖሎጂን ያለአገባብ ለመጠቀም የሚሞክሩም ሆኑ የሚያዳፍኑ ከፈጣሪና ከተፈጥሮ ጋር የሚታገሉ ከቤተ ክርስቲያናችን መርሆ ጋራ የሚጋጩ ናቸው:: በነገረ መለኮት ጥናታችን መሠረት ይህን ሰብአዊ ክሂሎትና ተኬነወት እየሰነጠቀ ማለፍ ያለበት (ነገረ መለኮት) ዶክትሪን ብቻ ነው::

ሰው ዛሬ እመቀ-እመቃትን አየረ-አየራትን የሚፈነቃቅልበት ረቀው-ርቀው የማይታዩትን አጽራረ-ሰብና ፍቁራነ-ሰብ ፍጥረታትን ጎትቶ እያቀረበና እያጎሏ በመየት፥ ጠላት የሆኑትን አሚከላዎች-ተሐዋስያንን እየለየ የሚመታበትና የሚአጠቃበት፥ ወዳጁ የሆኑትን ተሐዋስያን የሚጠብቅበትና የሚጠቀምበት መሳሪያው የጠራው ቴክኖሎጂ ነው:: ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አበው በአተረጓጎም ስልታቸው ያስተማሩንን እየተረዳን የምንራመድ ከሆን፥ ሥራችን ክፉ ሆኖ መጋለጥን የምንፈራ ካልሆን በቀር፥ ሰባዊ ባሕል ከወለደው ከቴክኖሎጂ ጋር የሚያጋጨንና ሕዝባችንንም ከዚህ እንድናርቅ የሚአደርገን አንዳችም ነገር አይኖርም::

## ማጠቃልያ:-

የዚህች ጦማር ዋና ዓላማ ከነገረ መለኮቱ ጋራ ጎን ለጎን የተቀመጠችውን "አብጅ" የምትለዋን አምላካዊ ትእዛዝ ከምን ተነስታ ከየት እንደደረሰች ለመግለጽ መሆኑን ለአንባቢ እያስገነዘብኩ፥ ዛሬ በጣያት አምላኪዎች ተበጅቶ፥ በአቡነ ጳውሎስ ተባርኮ በቅድስት መዲናችን የቆመው ሐውልት "አብጅ" በምትለው ርእስ የሚካተት ስለሆነ፥ ተበጅተው በአገራችን ከቆሙት ሐውልታት ጋር በማነጻጸር፥ አቡነ ጳውሎስ ባርከውት ስለቆመው ሐውልትና እራሳቸውም ስለሚያበጁት ትንሽ ተናግሬ ይህችን ጦማር ለማጠቃለል እሞክራለሁ::

ዛሬ በውስጥም በውጭም በሰፊው ሲነገር የምንሰማው አስቀድማ የነቃች ኢትዮጵያ አገራችንን በመምራት ላይ ያለው የኢሐደግ መንግስት፥ የዘመናችን ተኬንዎት ያበጀውን የመገናኛ መስመሮችን ሁሉ ለመዝጋት የአገሪቱን ሐብት ከሚራበው ሕዝብ አፍ እየፈለቀቀ በማፍሰስ ላይ ነው:: ከላይ በተገለጸው ያተረጓጎም ስልት እያስተማረች ባሳደገችን በቤተ ክርስቲያናችን ራስ ላይ የተቀመጡት ፓትርያርክ ይህን ተግባር ከመገሰጽ ይልቅ፥ እንዲአውም እራሳቸው ብሰው "እስመ ኢየአምርዋ ለጽድቀ እግዝአብሔር: አላ ፈቀዱ በጽድቀ ርዕሶሙ ይቁሙ:: ወለጽድቀ እግዚአብሔር ስእኑ ኀኒየ" (ሮሜ ፲:፫) እንዳለው፥ የቤተ ክርስቲያናችንን ነገረ መለኮትና ቀኖና ደምስሰው በተቀደሰችው ምድራችን ላይ የድንጋይ ሐውልት በራሳቸው ምስል ተበጅቶ ሲቆም ተስማሙ::

በወንድ ሐፍረተ ሥጋ አምሳል ተበጅቶ አክሱም ላይ የተተከለው ሐውልትም እኮ፥ ዝርዝር ሀተታው አሁን ካቀረብኩት ሐሳብ ጋራ ስለማይስማማ ልለፈው እንጅ፥ የሚናገረውና የሚአንጸባርቀው፥ የጠለቀ፥ የረቀቀ፥ የሞራልና የሥነ ልቡና መልእክት አለው:: ያጼ ምንይልክ ሐውልትም፥ በጥንተ አብሶ ተልዕኮ ኢትዮጵያን የወረረውን ጠላት የመታ፥ ነጻነትን ለተጠማ ሕዝብ ነጻነትን የሚሰብክ፥ የሰባዊ ልዕልና ክብርና ሞገስ ምንጭ ነው:: ያቡነ ጴጥሮስ ሐውልትም የቆመው፥ ደማቸው በፈሰሰባት ምድር ነው:: በእጃቸው ላይ የሚታየው ሰንሰለት ነው:: በፊታቸው ተደቅኖ የሚታየው የተገደሉበት መትረየስ ነው:: ሐውልቱ የተበጀላቸው ላርበኝነታቸው እንጅ ለክህነታቸው አይደለም:: በስተጀርባው የተሸከመው መልእክት፥ እመቤታችን ከሰውነት የሚአወጣትን ጥንተ አብሶ በሚል ስም እየሰበከ፥ የክርስቶስን ፍጹም ተዋሕዶን እየደመሰሰ፥ ድንበር እያፈረሰ፥ የኢትዮጵያውያንንን ደም እያፈሰሰ፥ የሕዝቡን ስነ ልቡና እየገሠሠ የመጣውን፥ የሮማ ፓፓ ባርኮ ያዘመተውን የሞሶሊኒን ግፍና ጭካኔ የሚአሳይ ነው:: አገራችንን ለመንበርኘት ለሚመጣው ሁሉ የወቀሳና የከሰሳ ድምጽ የሚአሰማ ነው:: ለኢትዮጵያ ልጆች ደግሞ በመንፈስ በሞራልና በታማኝነት ነቅተን እንድንኖር የሚሰብክ ሐዋርያ ነው::

የሚናደፉትን የእባቦችን ምስል እንዲአሳዩ ሆኖ በአቡነ ጳውሎስ ምስል የተበጀው ሐውልት የኦርቶዶክሳዊውን ያተረጓጎም ስልት ስቷል:: ይልቁንስ እንደጣሊያኖች ወታደር፥ የመንግሥታቸው ወታደር ኢትዮጵያውያንን በጥይት እየነደፈ ሲገድል፥ ጣሊያኖች ባቡነ ጴጥሮስ እጅ ላይ የከተቱን ሰንሰለት በኀብርቱካን እጅ ላይ ሲገባ መስማማታቸውን ለማንጸባረቅ ካልሆነ በቀር፥ አባቶቻችን ካስተማሩን ከኦርቶዶክሱ ያተረጓጎም ስል ጋራ የሚአገናኘው ስልት የለውም:: ያቡነ ጴጥሮስ ሐውልት የመነጨው የራሳቸው ደም በፈሰሰበት፥ የአቡነ ጳውሎስ ሐውልት ተበጅቶ የቆመው የኢትዮጵያውያን ደም በፈሰበት ላይ ነው:: የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት በሕያው ታሪኩ ዛሬም እየተናገረ ነው:: በሕይወት እያሉ የተበጀው የአቡነ ጳውሎስ ሐውልት ግን፥ በሕይወት እያሉ ለሚጠየቁት ጥያቄ የማይመልሱ በመሆናቸው ካቆሙት የድንጋይ ሐውልት የማይሻሉ ናቸው ብል፥ በያሉበት ሆነው ቅሬታቸውን የሚያሰሙት ኢትዮጵያውያን ይቅሩና፥ የአኀት አብያተ ክርስቲያናት አባላት እንኳ ተሳስተሀል የሚሉኝ አይመስለኝም::

ይህ ሐውልት የሳቸውን ባሕርይ ብቻ የሚአንጸባርቅ አይደለም:: "ይደለወከ ትትመሐር ግብረ እድ በዘተሐዩ ቦቱ: ከመ ኢታክብድ ፆረ ላዕለ አኀው: ወተገበር በዓስብ ምስለ ካልዕ ከመ ትርከብ ሲሳየ ዕለት"(ሃይ አው ምዕ ፳፩: ፴፬) ማለትም:-"አንተ መነኩሴ! ገንዘብ ከሰው እንዳትቀበል:: የዕለት ምግብ ለማግኘት የሚያስችልህን እደ ጥበብ (ማበጀት) ተማር!" የሚለውን ሥርአተ ገዳም ሰርዘው ምእመናኑን እየዘሩ እንዲዘርፉ በራሳቸው ባሕርይ፥ እንደራሳቸው ሐውልት እየቀረጹ ያሰማሯቸውን ሁሉ ጳጳሳትና፥ መነኮሳት የሚወክል ነው::

በአገራችን ውስጥ ያላችሁ፥ በውጭም ተበትነን ያለን ሁሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ሆይ! "ዘዐቢይ በተኬንወቱ ወኃያል በምግባሩ ወጠቢብ በምክሩ ወጽኑዕ በኃይሉ:: ዘህልው ውስተ ኩሉ ምስለ ኩሉ::"(ቅዳሴ ገጽ ፺፯ የሚለውን እንደመመሪያ እየተጠቀምን፥ በነቅዕ፥ በፈለግ፥ በተቀረጸው ተዋሕዷዊ መንፈስ፥ ንጹሑን የተዋሕዶውን ነገረ መለኮት ከውጭና ከውስጥ አፈ ታሪክ ለይተን ለመጠበቅ ከመቸውም የበለጠ ጥረት ማድረግ አለብን:: ይልቁንም የተሳሳቱ መሪዎች በምድራችን ላይ የሚአቆሙትን ጣዖት እያፈረስን፥ የጠራውን የማበጀት (ቴክኖሎጂ) ክንውን፥ ባባቶቻችን ያተረጓጎም ስልት እያቀሰስን የነገረ መለኮቱ አክባሪና ተሸካሚ ቄስ ልናደርገው የደረስንበት ዘመን ይጠይቀናል::

በተረፈ "ጠብቅ" በምትለዋ ርእስ አዘጋጅቼ በማቀርባት ጦማር ለመገናኘት ያብቃን::

ይቆየን

ማሰሰቢያ:-

"አሥራግ" በመባል የሚፈረጁት ከአንቅዕትና (ብሉይና ሐዲስ) ከአፍላግ (በነዮሐንስ አፈወርቅ እና በሰለስቱ ምዕት የተደረሱ) ሳይወጡ ሊቃውንት በዘመናቸው ለገጠማቸው ችግር የጻፏቸው መጻሕፍት ናቸው::